# ምዕራፍ አንድ ፡

## ሙከራ ጥያቄ አንድ

I. የሚከተሉትን ጥያቄዎች እውነት ወይም ሀሰት በማለት መልሱ

1. ፍፁማዊ መገኛ በአካባቢ ከሚገኙ ተፈጥሮአዊ ወይም ሰው ሰራሽ ነገሮች ጋር በማነፃፀር የሚገለፅ የአንድ ነገር መገኛ ነው::
2. ኢትዩጵያ የባህር በር ካላቸው ሀገሮች ውስጥ የምትመደብ ሀገር ናት፡
3. የኢትዮጵያ  ፍጹማዊ መገኛ 3 ዲግሪ ሰሜን እና 25 ዲግሪ ሰሜን እንዲሁም ከ 33 ዲግሪ ምስራቅ እና 48 ዲግሪ ምስራቅ ነው::
4. ከሰሜን እስከ ደቡባዊ ጫፍ ድረስ የኢትዮጵያ መገኛ 12 ዲግሪ ኬክሮስ ነው ፡
5. ኢትዮጵያ ከጀቡቲ በስተ ደቡብ በኩል ትገኛለች ፡
6. ኢትዮጵያ በስተ ደቡብ ምስራቅ የምትዋሰነው ኬንያ ጋር ነው::
7. የኢትዮጵያ አዋሳኝ ሀገሮች ብዛት ስድስት  ናቸው::

LIVEWORKSHEETS

8. ኬክሮስን እና ኬንትሮስን በመጠቀም የአንድን ቦታ መገኛ የምናሳይበት መንገድ

   አንፃራዊ መገና ይባላል፡፡

9. በፍፁማዊ መገኛ የአንድን ቦታ መገኛ በአሃዝ ልኬት ለመግለጽ ይቻላል፡፡

10. የአንድን ሃገር መገኛ የሚያዋስኑትን ሀገሮች በመጠቀም በፍፁማዊ መገኛ መግለጽ ይቻላል ፡

11. ፍጹማዊ መገኛ አንድን ቦታ በየብስ ወይም በውሃ ክፍል የሚገለጫ ዘዴ ነው ፡

## II. በ “ሀ” ረድፍ ከተቀመጡት ሀገሮች የኢትዮጵያን አንፃራዊ መገኛ በ “ለ” ረድፍ ከተቀመጡት ጋር በማዛመድ ትክክለኛውን ቁጥር በባዶ ቦታው ላይ አስቀምጡ

| ሀ | ለ |
|---|---|
| 1. ኬን ያ | ..............በስተ ደቡብ ምዕራብ |
| 2. ጂቡቲ | ..............በስተ ደቡብ |
| 3. ሱዳን | ................ በስተ ሰሜን |
| 4. ኤርትራ | ............... በስተ ሰሜን ምስራቅ |
| 5. ሶማሊያ | ............... በስተ ምዕራብ |
| 6. ደቡብ ሱዳን | ............... በስተ ደቡብ ምስራቅ |

## III. ለሚከተሉት ጥያቄዎች ትክክለኛውን መልስ ምረጡ

LIVEWORKSHEETS

1. በይዘት ቀለል የተደረገ፣ መጠኑ ያነሰ እና በዝርግ ወረቀት ላይ ከላይ ወደታች በምድር ላይ ያሉ ቦታዎችን በከፊልም ሆነ ሙሉ በሙሉ የምናሳይበት መሣሪያ ምን ይባላል ?

2. ከሚከተሉት ውስጥ የኢትዮጵያ አዋሳኝ ሀገር ያልሆነው የትኛው ነው ?

ሀ) ኬን ያ ለ) ጂቡቲ ሐ) ግብጽ መ) ሱዳን

3. በሳተላይት አማካኝነት ዓለማቀፋዊ በሆነ ሁኔታ ቦታዎችን የምናሳይበት ዘዴ የትኛው ነው ?

ሀ) ጂፒኤስ ለ) ጉግል ኧርዝ ሐ) ጎግል ካርታ መ) ካርታ

4. ከሚከተሉት ውስጥ የ ጂ.ፒ.ኤስ ጥቅም ያልሆነው የቱ ነው ?

ሀ) ተጓዦች በአየር፣ በባህር እና በመሬት ያሉበትን እና የሚሄዱበትን ቦታ ይለዩበታል።

ለ) አንድ ቦታ ከሌላ ቦታ የሚገኝበትን ርቀት ለማወቅ ያስችላል፡፡

ሐ) የሰዎችን እንቅስቃሴ ለማወቅ ይረዳል፡፡

መ) የአንድን ቦታ ፍፁማዊ መገኛ ለማወቅ ያስችላል

ሰ) የተለያዩ ካርታዎችን ለማዘጋጀት ይረዳል፡፡

5. የሳተላይት ምስሎችን፣ የአየር ላይ ፎቶግራፎችን፣ የጎዳና ካርታዎችን የሚያካትት መተግበሪያ ምን ይባላል?

ሀ) ጂፒኤስ ለ) ጉግል ኧርዝ ሐ) ጎግል ካርታ መ) ካርታ

6. እጅግ በጣም የታወቀ እና በስፋት ጥቅም ላይ የዋለ ጂኦግራፊያዊ የመረጃ ስርዓት መተግበርያ ነው፡፡

ሀ) ጂፒኤስ ለ) ጉግል ኧርዝ ሐ) ጎግል ካርታ መ) ካርታ

7. ከሚከተሉት ውስጥ ንድፍ ካርታ ለመስራት የሚያስችሉ መመሪያዎች ያልሆነው የትኛው ነው ?

LIVEWORKSHEETS

ሀ) ካርታዎቻቸው የሚዘጋጁ ቦታዎችን መለየት

ለ) የቦታዎችን መነሻ እና መድረሻ ማስቀመጥ

ሐ) የቦታውን ንድፍ ካርታ በሀሳብ ማስቀመጥ

መ) የሚሳለውን ካርታ ድንበር መወሰን

ሰ) የድንበሩን መስመሮች በመከፈል በአራት ማዕዘን ቦታውን ማስቀመጥ

8. ካርታ አዘጋጆችን መረጃን እንዲፈጥሩ፣ እንዲያከማቹ፣ እንዲመለከቱ እና መስተጋብር እንዲፈጥሩ የሚያስችለው መተግበሪያ የትኛው ነው ?

ሀ) ጉግል ኧርዝ ሐ) ጎግል ካርታ ሀ) ጂፒኤስ መ) ሀ እና ለ

9. የኢትዮጵያ ፍጹማዊ መገኛ ከሰሜን እስከ ደቡባዊ ጫፍ ድረስ ስንት ዲግሪ ነው ?

ሀ) 12 ዲግሪ የኬክሮስ (Latitudes) ለ) 15 ዲግሪ የኬንትሮስ (Longitudes)

ሐ) 12 ዲግሪ የኬንትሮስ (Longitudes) መ) 15 ዲግሪ የኬክሮስ (Latitudes)

10. የኢትዮጵያ ፍጹማዊ መገኛ ከምሥራቃዊ ጫፍ እስከ ምዕራባዊ ጫፍ ድረስ ስንት ዲግሪ ነው ?

ሀ) 12 ዲግሪ የኬክሮስ (Latitudes) ለ) 15 ዲግሪ የኬንትሮስ (Longitudes)

ሐ) 12 ዲግሪ የኬንትሮስ (Longitudes) መ) 15 ዲግሪ የኬክሮስ (Latitudes)

11. ከሚከተሉት ውስጥ ከኢትዮጵያ የኬንያ አንፃራዊ መገኛ የሆነው የቱ ነው?

ሀ) በስተ ደቡብ ለ) በስተ ደቡብ ምዕራብ

ሐ) በስተ ምዕራብ መ) በስተ ሰሜን

12. ኢትዮጵያን በስተ ሰሜን ምዕራብ በኩል የሚያዋስናት ከሚከተሉት የትኛው ሀገር ነው?

ሀ) ሱዳን ለ) ቀይ ባህር ሐ) ጂቡቲ መ) ኤርትራ

LIVEWORKSHEETS